**እስትንፋሰ - እግዚአብሔር ያለበትን መጽሐፍ ቅዱስ እንዳመሰግን የሚያደርጉኝ 10 ምክንያቶች**

1. የመታዘዝ ሁሉ ምንጭ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እምነትን ይቀሰቅሳል።
   - እንግዲያስ እምነት የሚገኘው መልእክቱን ከመስማት ነው፤ መልእክቱም በክርስቶስ ቃል ነው። (ሮሜ 10፡17)

2. መጽሐፍ ቅዱስ ከሐጢአት ነጻ ያወጣል።
   - እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም ነጻ ያወጣችኃል። (ዮሐንስ 8:32)

3. መጽሐፍ ቅዱስ ከሰይጣን ነጻ ያወጣል፡፡
   - የጌታም አገልጋይ ሊጣላ አይገባውም፤ ይልቁን ለሰው ሁሉ ገር፣ ለማስተማር ብቃት ያለው፣ ትዕግስተኛም መሆን ይገባዋል፤ እውነትን ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ንስሐን እንደሚሰጣቸው ተስፋ በማድረግ የሚቃወሙትን በየዋህነት የሚያቀና መሆን ይኖርበታል፤ ይኸውም ወደ አእምሮአቸው ይመለሳሉ፤ ፈቃዱን ሊያስፈጽማቸው ምርኮኛ አድርጎ ከያዛቸው ከዲያብሎስ ወጥመድም ያመልጣሉ በማለት ነው። (2ጢሞ2፡ 24-26)

4. መጽሐፍ ቅዱስ ይቀድሳል።
   - ቃልህ እውነት ነው፤ በእውነትህ ቀድሳቸው። (ዩሐንስ 17፡ 17)

5. መጽሐፍ ቅዱስ ከምግባረ ብልሹ ሕይወት ነጻ አውጥቶ እግዚአብሔርን መምሰል ያጎለብታል።
   - በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኃይል ሰጥቶናል። ከክፉ ምኞት የተነሣ በዓለም ካለው ምግባረ ብልሹ ሕይወት አምልጣችሁ ከመለኮታዊ ባህርይ ተካፋዮች እንድትሆኑ በእነዚህ ነገሮች አማካይነት እጅግ ታላቅና ክቡር የሆነውን ተስፋ ሰጥቶናል። (2ጴጥሮስ 1፡3-4)

6. መጽሐፍ ቅዱስ ፍቅርን ያገለግላል።
   - ፍቅራችሁ በጥልቅ እውቀትና በማስተዋል ሁሉ በዝቶ እንዲትረፈረፍ እጸልያለሁ። (ፊልጵስዩስ 1፡9)
   - የዚህ ትእዛዝ ዐላማ ግን ከንጹሕ ልብ፣ ከበጎ ኅሊና እንዲሁም ከእውነተኛ እምነት የሚገኝ ፍቅር ነው። (1ጢሞ 1፡5)

7. መጽሐፍ ቅዱስ ያድናል።
   - ለህይወትና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፤ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ፣ ራስህንና የሚሰሙህንም ታድናለህና። (1ጢሞቴዎስ 4፡16)
   - ስለዚህ ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ መሆኔን በዚች ቀን እመሰክርላችኋለሁ፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሁሉ ለእናንተ ከመግለጽ የተቆጠብሁበት ጊዜ የለምና። (ሐዋ 20፡26-27)
   - እንዲሁም ይድኑ ዘንድ እውነትን ባለ መውደድ የሚጠፉትን ሰዎች በሚያታልል በተለያየ የክፋት ሥራ ይመጣል። (2ተሰሎንቄ 2፡10)

8. መጽሐፍ ቅዱስ ደስታን ይሰጣል።
- ደስታዬ በእናንተ እንዲሆንና ደስታችሁም ሙሉ እንዲሆን ይህን ነግሬአችኋለሁ። (ዮሐንስ 15፡11)

9. መጽሐፍ ቅዱስ ጌታን ይገልጠዋል።
- እግዚአብሔር በሴሎ ይገለጥ ነበር፤ በዚያም በቃሉ አማካይነት ራሱን ለሳሙኤል ገለጠ። (1ሳሙኤል 3፡21)

10. ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የቤቱ፣ የህይወቱ፣ የአገልግሎቱና ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሆነው ዘላለማዊ ተስፋዬ መሰረት ነው።